# ምሥጢረ ጥምቀት

## ጌታ ለምን በዮርዳኖስ ተጠመቀ?

### 1ኛ. ቀድሞ የተነገረውን ትንቢት ሊፈጽም ነው

ልበ አምላክ ዳዊት ጌታ ሰው ከመሆኑ ከሺህ ዘመን ቀደም ብሎ የጌታ ጥምቀት በዮርዳኖስ እንደሚሆን ትንቢት ተናግሯል፡፡ ‹‹ባሕር አየች ሸሸችም፡፡ ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ፡፡ ተራሮች እንደ ኮርማዎች፣ ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ፡፡ አንቺ ባሕር የሸሸሽ፣ አንቺም ዮርዳኖስ ወደ ኋላሽ የተመለስሽ ምን ሆናችኋል? እናንተም ተራሮች እንደ ኮርማዎች፣ ኮረብቶችስ እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ? ከያዕቆብ አምላክ ፊት›› (መዝ.133/114፣3-7)፡፡

### 2ኛ. ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ ነው

ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ (ምንጩ) አንድ ነው ዝቅ ብሎ በደሴት ይከፈላል፣ ከታች ወርዶ ደግሞ ይገናኛል፡፡ ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ እንደሆነ የሰው ሁሉ ምንጩ አንድ አዳም የመሆኑ፤ ዝቅ ብሎ በደሴት መከፈሉ እስራኤል በግዝረት፣ አሕዛብ በቁልፈት የመለያየታቸው፤ ከታች ወረድ ብሎ መገናኘቱና ጌታም በመገናኛው ላይ መጠመቁ ሕዝብና አሕዛብን በጥምቀቱ አንድ ሊያደርግ መምጣቱን ያጠይቃል፡፡

ኢዮብ ከደዌው የዳነው በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ነው፡፡ ኢዮብ የአዳም ምሳሌ፤ ደዌ የመርገመ ሥጋ፣ የመርገመ ነፍስ፤ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ነው፡፡ የአዳም ዘር ከማኅጸነ ዮርዳኖስ ዳግም ተወልዶ ከመርገመ ሥጋና ከመርገመ ነፍስ ይላቀቃል፡፡

እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል፡፡ ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ፡፡

ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ብሔረ ሕያዋን አርጓል፤ ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ፡፡

የኤልሳዕ ደቀ መዛሙርት ‹‹እነሆ በፊትህ የምንቀመጥበት ሥፍራ ጠብቦናል ወደ ዮርዳኖስም እንሂድ ከእኛም እያንዳንዱ ከዚያ ምሰሶ ያምጣ፣ የምንቀመጥበትንም ሥፍራ በዚያ እንሥራ›› አሉት፡፡ እርሱም

መምሕረ ትሕትና ነውና አብሯቸው ሄደ፡፡ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሲቆርጥ ምሳሩ ከዛቢያው ወልቆ ከባሕር ገባበት፡፡ ‹‹ጌታዬ ጥንቱን የተውሶ ያውም ጠፋ ተጨርሶ›› አለው፡፡ የገባበትን አሳየኝ ብሎ የዛፍ ቅርፊት ቀርፎ አመሳቅሎ ቢመታው መዝቀጥ የማይቻለው የዛፍ ቅርፊት ዘቅጦ መዝቀጥ የሚገባውን ብረት ይዞት ወጥቷል፡፡ ይህም ሞት የማይገባው ጌታ ሞቶ፣ ሞት የሚገባው አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ነው፡፡

ንዕማን በዮርዳኖስ ተጠምቆ ከለምጹ ተፈውሷል፡፡ እናንተም በማኅፀነ ዮርዳኖስ ተጠምቃችሁ ከኃጢአት ከጉስቁልና ትነጻላችሁ›› ሲል በዮርዳኖስ ተጠምቋል፡፡

**3ኛ. የዕዳ ደብዳቤያችንን ይቀድልን ዘንድ ነው፡፡**

ጌታ ወደ ዮርዳኖስ ሄዳ የተጠመቀበት ምሥጢሩ ዲያብሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ በአባታችን በአዳምና በእናታችን በሔዋን ላይ ሥቃይ አጸናባቸው፡፡ ‹‹ስመ ግብርናችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ ፍዳውን ባቀለልሁላችሁ ነበር›› አላቸው፡፡ እነርሱም ‹‹አዳም የዲያብሎስ ባርያ፣ ሔዋን የዲያብሎስ ገረድ›› መሆናቸውን አመኑለት፡፡ ይህን በሁለት ዕብነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎታል፡፡ በዮርዳኖስ የጣለውን (ጌታ) ሲጠመቅ እንደ ሰውነቱ ተረግጦ፣ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል፡፡ በሲዖል የጣለውን በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲያወጣ አጥፍቶላቸው ወጥቷል (ቆላ.2÷13-15)፡፡

የምሥጢረ ጥምቀት ትምህርት ከረኸሙ ባጭሩ፣ ከብዙው በጥቂቱ እነሆ ተፈጸመ፡፡ ወስብሐት ለእግአብሔር፡፡